OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የስነ-ጥበባት በመናፈሻዎች 2027 መመሪያዎች

ማመልከቻ የሚከፈተው፡- ሴፕቴምበር 15፣ 2026
**ማመልከቻ የሚዘጋው፡- ኦክቶበር 27፣ 2026፣ ከሰዓት 5 ሰዓት ላይ በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር**

## የገንዘብ ድጎማው አጠቃላይ እይታ

የስነ-ጥበባት እና ባህል ቢሮ (OAC) እና የሲያትል ፓርኮች እና መዝናኛ (SPR) ግለሰብ አርቲስቶች፣ የፈጠራ ባለሙያዎች፣ የማህበረሰብ ቡድኖች እና ድርጅቶች በሲያትል ከተማ በሚተዳደሩ ፓርኮች ውስጥ ከሜይ እስከ ኦክቶበር 2027 በሚከናወኑ የጥበብ እና ባህል እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮሩ የፕሮጀክት ሀሳቦችን እንዲያቀርቡ ይጋብዛሉ።

በማመልከቻ ሒደቱ ላይ ተጨማሪ መረጃ እና ድጋፍ ለማግኘት፣ የተደራሽነት ፍላጎቶችን ለማሳወቅ ወይም በተዘጋጀ የማመልከቻ ረቂቅ ላይ አስተያየት ለመቀበል **የድጎማዎች የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ Zach Frimmelን** በስልክ መስመር **206-963-9226** ወይም Zach.Frimmel@seattle.gov ማነጋገር ይችላሉ።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪዲዮ አማካኝነት) ጨምሮ፣ በእርስዎ ቋንቋ ሊያነጋግሩዎት የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** በስልክ መስመራችን በመደወል የሚናገሩትን ቋንቋ ያሳውቁን። አስተርጓሚ ወደ ስልክ ጥሪው እስኪቀላቀል ድረስ ጥቂት አፍታ ሊኖር ስለሚችል ይታገሱን።

## ማመልከቻ

በሲያትል ከተማ የድጎማ ድረ-ገጽ በኩል ማመልከቻዎን በበይነመረብ ማቅረብ ይችላሉ።

የኮምፒውተር ወይም የበይነመረብ አገልግሎት ከሌልዎት፣ በተቻለ ፍጥነት የቢሮውን ሠራተኞች ያናግሩ።

## ማመልከቻ የማስገቢያ ቀነ ገደብ

**ማክሰኞ፣ ኦክቶበር 27፣ 2026፣ ከሰዓት 11:00 ሰዓት ላይ በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር**

## የብቁነት መስፈርቶች

የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ ለዚህ ድጎማ ማመልከቻ ለማቅረብ ብቁ ይሆናሉ፡-

- በሲያትል ከተማ ውስጥ በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ በኪነጥበብና ባህል ላይ ያተኮሩ ህዝባዊ ሁነቶችንና እንቅስቃሴዎችን የሚያዘጋጁ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም የማህበረሰብ አደረጃጀት አባል መሆን አለብዎት።
- በኪንግ ካውንቲ (ወይም በኪንግ ካውንቲ ያልተካተቱ አካባቢዎች) ውስጥ በስምዎ የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት አድራሻ ወይም የንግድ ቦታ አድራሻ ወይም ቋሚ የስቱዲዮ/የሥራ ቦታ አለዎት። የፖስታ ሣጥን ቁጥር መሆን የለበትም። አድራሻዎ ለድጋፍ ብቁ መሆኑን ለመመልከት ይህን የፍለጋ መሣሪያ መጠቀም ይችላሉ።
- የፌደራል ግብር ከፋይ መታወቂያ ቁጥር (Federal Tax ID number)፣ የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (Social Security Number)፣ (ITIN)፣ ወይም የሠራተኛ መታወቂያ ቁጥር) ሊኖርዎ ይገባል።

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሁኔታዎች የሚመለከትዎት ከሆነ ለዚህ የፋይናንስ ድጋፍ (ግራንት) ማመልከት አይችሉም፡-

- ከታህሳስ 31, 2026 በኋላ ክፍት የሆነ (ያልተጠናቀቀ) የ-Arts in Parks ውል ካለዎት።

- ለተመሳሳይ ፕሮጀክት ወይም ወጪዎች ከሲያትል ከተማ አስተዳደር የገንዘብ ድጋፍ የተቀበሉ ከሆነ። ይህ ከስነ-ጥበብና ባህል ቢሮ (OAC) ወይም ከፓርኮችና መዝናኛ መምሪያ (SPR) የሚገኙ ሌሎች የገንዘብ ድጋፎችን ያጠቃልላል።
- ከስነ-ጥበብና ባህል ቢሮ (SPR) የ2027 Get Moving፣ Recreation For All፣ ወይም Hope For Youth የገንዘብ ድጋፍ የተቀበሉ ከሆነ።

## የገንዘብ ድጋፍ

ከ**$2,000-$8,000.** ዶላር ማመልከት ይችላሉ።

## የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች

ስለዚህ የፋይናንስ ድጋፍ ፕሮግራም ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እና ብቁ የሆነ ማመልከቻ አዘጋጅተው ለማቅረብ የሚከተሉትን መመሪያዎች ይመልከቱ። ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱ ሰዎች እንዲሳተፉ እናበረታታለን።

### ክፍለ-ጊዜ 1 - በቨርቹዋል የሚካሄድ

ሰኞ፣ ሴፕቴምበር 21፣ ከሰዓት 4:00-5:30 በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
ቨርቹዋል (በኦንላይን)፡- Microsoft Teams
ለሴፕቴምበር 21 ስብሰባ ቦታ ይያዙ

### ክፍል 2 - በአካል የሚካሄድ

ሐሙስ፣ ኦክቶበር 8፣ ከምሽቱ 6:00-7:30 በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
በአካል፡- Garfield የማህበረሰብ ማዕከል
ኦክቶበር 8 ስብሰባ ቦታ ይያዙ

### የረቂቅ ማመልከቻ ግምገማ

ይፋዊ ማመልከቻዎን ከመላክዎ በፊት፣ በማመልከቻ ቅጹ አንድ የተመረጠ ክፍል ላይ የባለሙያ አስተያየት እና ግምገማ ለማግኘት ለአንድ ጊዜ የሚሆን ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ጥያቄዎን እስከ ማክሰኞ፣ ኦክቶበር 6፣ 2026 ድረስ በኢሜይል ወደ Zach.Frimmel@seattle.gov ይላኩ።